አዲስ ነገር ጋዜጣ አንድነት ፓርቲን ከምስረታው ጀምሮ በ”ልሳንነት” ሲያገለግል ነበር፡፡እውነተኛውን ከለር ሲያይ እሱም “የለሁበትም” እያለ ነው መሰል…



«ያለምት ቀሪ ሒሳብ. . .»

መስፍን ነጋሽ

በነገራችን ላይ

የአንድነት ምስቅልቅል ጉዞ

አብርሃም በጊዜው

ከሦስት ሳምንት በፊት ነው፤ የደብረ ማርቆስ አየር በመቀዝቀዙ በመንገድ ላይ የሚዘዋወር ሰው ብዙ አይታይም። የከተማይቱ ነዋሪ እና የአነስተኛ ሱቅ ባለቤት የኾነው ዮሐንስ ዘለቀ ሰሞኑን እረፍት ከነሳው የዕቃ መወደድ እኩል የአገሪቱ ፖለቲካ ያስጨንቀዋል። የአንድነት ለዲሞክራሲ እና ለፍትሕ ፓርቲ አመራሮች ደብረማርቆስ መግባታቸውን ሲሰማ ለሚያስጨንቀው ጉዳይ ምላሽ ለማግኘት የዕለተ ሰንበት ቀጠሮውን በከተማው ሲኒማ አዳራሽ ለማድረግ ቀጠሮ ይዟል።

ቀጠሮውን አክብሮ ከተገኘበት የአንድነት ስብሰባ ግን ሁሌም የሚያስጨንቀውን ጥያቄ ሳያቀርብ አልወጣም። የቅንጅት ፓርቲን ይደግፍ የነበረው ዮሐንስ «ላለመከፋፈላችሁ ምን ዋስትና ትሰጡናላችሁ?» ሲል ለአንድነት አመራሮች ጥያቄውን ሰነዘረ። ስብሰባውን ይመሩ የነበሩት የድርጅት ጉዳይ ሐላፊው እና ምክትል ሊቀመንበሩ ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው እንዲሁም የሰሜን ቀጠና አስተባባሪ አቶ ይልቃል ጌትነት ምላሽ ያሉትን ሰጥተዋል።

ኢንጅነር ግዛቸው እና አቶ ይልቃል በደብረማርቆስ በአንድ ሐሳብ ሲናገሩ ቢቆዩም አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በሁለት ጎራ ተከፍለዋል። አቶ ይልቃል የሚገኙበት እና የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት አባል የኾኑትን ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የያዘው ጎራ በበተነው ጽሑፍ የአንድነት አመራሮችን ይተቻል። «የአንድነት ሥራ አስፈጻሚ አንድ አባል አንድ አምሳል ኾኖ የአንድነትን መሠረታዊ ዓላማ ፈጽሞ የሳተ የአመራር ስልት በመከተል ፓርቲውን በጣም የከፋፈለው እና ወደ አደገኛ ደረጃ ያደረሰው መኾኑን በግልጽ እያየን ነው» ይላል።

አመራሩ በሦስት የተባሉ መሠረቶች ላይ እየተንከባለለ እንደሚገኝ የሚገልጸው ይህ ጽሑፍ «በዘፈቀደ የጉልበት አሠራር በማስደንገጥ እና በማስበርገግ»፣ «የፓርቲውን ገንዘብ በመናኘት ታማኝ ሎሌዎችን በመግዛት» እንዲሁም «በወዳጅነት (በጓደኝነት) ሚና አብሮው የሚቆሙትን በማሰባሰብ እድሉ ይፈፀማል» በሚል ይኮንናል። ጽሑፉ «አስተዳደራዊ በደሎች ተፈጽመዋል» ሲልም የሥራ አስፈጻሚውን ይከሳል።

«ይህ የኾነው በፓርቲው ውስጥ ግልጽ የኾነ አሠራር ባለመፈጠሩ ነው» የሚሉት አቶ ይልቃል «የአስተዳደር ብልሹነት የፖለቲካ ተጽዕኖ ይፈጥራል» ሲሉ ያስረዳሉ። አቶ ይልቃልን ጨምሮ 20 የምክር ቤት አባላት የያዘው ቡድን የሚያሰማው ቅሬታ ግን በአመራሩ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

«መዋቅራዊ እና ዲሞክራሲያዊ ውይይትን የማይቀበሉ በተለይም ከመድረክ ጋራ አብሮ መሥራት የሚለው ሐሳብ የሚሰነፍጣቸው የተወሰኑ ግለሰቦች አፍራሽ ጽሑፍ በማዘጋጀት እና ከደንብ ውጭ በመበተን በአባላት መካከል ወዥንብር የመፍጠር ሙከራ አድርገዋል» ሲሉ የአንድነት ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ሐላፊ ዶክተር ኀይሉ አርአያ ቡድኑ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ይገልጻሉ።

የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በበኩሉ በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረውን መከፋፈል ለመግታት በሚል መግለጫ አውጥቷል። «የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በፓርቲው ላይ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ደንብ በሚፈቅድለት መሠረት ሕጋዊ ርምጃ በየደረጃው በመውሰድ ላይ ነው» ሲል በመግለጫው ገልጿል። ኾኖም የመጨረሻ ርምጃ የመውሰድ ሐላፊነት ያለው ብሔራዊ ምክር ቤቱ መኾኑን ፓርቲው ባወጣው መግለጫ አሳውቋል።

ኮሚቴው ይህን ቢልም የኻያ አንድ የምክር ቤት አባላትን ፊርማ በመያዝ የተበተነው ጽሑፍ «በሥልጣን መባለግ» የሥራ አስፈጻሚው አንዱ መገለጫው ነው ይላል። የሥራ አስፈጻሚው «ደንብ ተላልፎ ሰዎችን አግዷል፤ ሥልጣኑን ያለ አግባብ ተጠቅሟል» ሲል ጽሑፉ ይከሳል። በሥራ አስፈጻሚው እና በምክር ቤት አባላት መካከል የተነሳው አለመግባባት በሁለቱም ወገኖች የተለያየ ትርጉም ቢሰጠውም ጉዳዩ ከርሮ በቀጣይ የብሔራዊ ምክር ቤት ውሳኔ እየጠበቀ ይገኛል።

ጉዳዩን የተከታተሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ግን የአንድነት «ምስቅልቅል» የጀመረው አሁን እንዳልኾነ ይናገራሉ። «አንድነት የቅንጅት ወራሽ ነኝ የሚለው ድምፁ የቅንጅትን ችግሮች እንዲጋራ አድርጎታል» ይላሉ ታዛቢዎቹ። «ቅንጅትን ለማፍረስ ጥያቄ ሲነሳ የተፈጠረው ችግር መድረክ እና አንድነት አብረው ለመሥራት በተስማሙበት ወቅት ምልክቱን ሰጥቷል» ሲሉ ጉዳዩ በመድረክ ማኒፌስቶ ውይይት ጊዜ ጎልቶ መውጣቱን ይገልጻሉ። «መድረክ» ለአንድነት ምስቅልቅል እንደምክንያት ቢቀርብም ምክንያቱ ይህ ብቻ እንዳልኾነ ታዛቢዎች ይናገራሉ።

በሁለቱም ወገኖች የሚቀርቡት ችግሮች በግልጽ የሚስተዋሉ ናቸው ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ። የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ መምህሩ አቶ ሰሜር የሱፍ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል አለመዳበሩ ለዚህ መሳይ ንትርክ እና መከፋፈል እንደሚዳርግ ያስረዳሉ። መምህሩ የኢትዮጵያን የተቃውሞ ፖለቲካ «[illegible] የተሞላ ነው» ይሉታል። «እኛ ፖለቲካ ባህል ጥሩ ሰው የምንለው [illegible] የሚሰጡትን የሚቀበል ነው» ይላሉ።

የዚህ ፖለቲካ ባህል አለመዳበር አንድነትን «ላለመከፋፈላችሁ ምን ዋስትና ትሰጡናላችሁ?» የሚሉ ጥያቄዎችን ወደ ጎን እንዲገፋ እንዳደረገው ለፓርቲው ቅርበት ያላቸው ሰው ይናገራሉ። ይህን የተረዳ የሚመስለው ዮሐንስ ግን በደብረማርቆስ ስብሰባ ኢሕአዴግን በምሳሌነት አንስቶ ተጨማሪ ጥያቄ ለአመራሮቹ አቅርቧል።

የቅንጅት መሪዎችን መበታተን ያስታወሰው ዮሐንስ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ ኢሕአዴግ «በጥቅም ቅስቀሳ» በልጧቸዋል ይላል። ዮሐንስ የኢሕአዴግን «የጥቅም ፖሊሲ» በቤተሰብ ደረጃ መድረሱን አስታውሶ «የመጀመሪያውን አርባ አምስት ደቂቃ በፍፁም የበላይነት ተበልጣችኋል» ሲል ለአመራሮቹ ተናግሯል። «ቀሪውን አርባ አምስት ደቂቃ በምን ዐይነት ታክቲክ ልትጫወቱት አስባችኋል?» ሲል አመራሮችን የጠየቀው ዮሐንስ ምላሹን ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በተግባር አግኝቷል።